የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሰላሳ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፺፱
አዲስ አበባ ህዳር ፱ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32th Year No.99
Addis Ababa 18th November, 2024

**ማውጫ**

**ደንብ ቁጥር ፩፻፹፱/፪ሺ፲፯**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች አስተዳደርን ለመወሰን የወጣ ደንብ**

ገፅ…………………………………………… ፫ሺ፱፻፴፭

**CONTENT**

**REGULATION No. 189/2024**

**A REGULATION TO PROVIDE FOR THE ADMINISTRATION OF SPORT FACILITIES OF THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT**

Page……………………………………..……..….3935

## ደንብ ቁጥር ፩፻፹፱/፪ሺ፲፯

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች አስተዳደርን ለመወሰን የወጣ ደንብ

የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ በሚኖርበት፣ በሚማርበት፣ በሚሰራበት አካባቢ በስፖርታዊ እንቅስቃሴ ተሳታፊ የሚሆንበትን ሁኔታ ማመቻቸትና ለዚህም ዓላማ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እንዲስፋፉና እንዲጠበቁ ማድረግ በማስፈለጉ፤

## REGULATION No. 189/2024

## A REGULATION TO PROVIDE FOR THE ADMINISTRATION OF SPORT FACILITIES OF THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT

**WHEREAS,**

WHEREAS, it is found necessary to facilitate the participation of the community in different sport activities at residential areas, schools and working places and to this end to promote the expansion and preservation of sport facilities;

የአንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በየአካባቢው በብዛትና በጥራት መኖርና ፍትሐዊ አገልግሎት መስጠት የነዋሪውን በተለይም የወጣቱን ጤንነት ለመጠበቅ፣ አካል ለመገንባት፣ አዕምሮ በማበልጸግ ለሃገር እድገት አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ ለማስቻልና ስፖርቱ ለታለመለት ዓላማና ግብ እንዲውል ደረጃቸውን የጠበቁ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች የሚቋቋሙበትን፣ የሚተዳደሩበትን፣ ቁጥጥር የሚደረግበትን እና ሕጋዊ ጥበቃ የሚያገኙበትን ግልፅ፣ ውጤታማ፣ የተቀናጀና ተጠያቂነት ያለበት ተቋማዊ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፹፬/፪ሺ፲፭ አንቀጽ ፺፬ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩.አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች አስተዳደርን ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፩፻፹፱/፪ሺ፲፯" ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪.ትርጉም**

የቃሉ ወይም የሐረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው ፤

፪. **"ከተማ አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

WHEREAS, the availability of sport facilities in different areas in the required number and quality creates conducive environment for maintaining the health, enhancing physical fitness, cultivating the brain of the community and in particular the youth, and there by enable them to contribute for the development of the country; to achieve the objectives and ends of sport, it has been found necessary to issue institutional operation system which provides for the establishment, administration, regulation and legal protection of sport facilities that meet the required standards;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 94 of the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to Specify the Power and Duties of the thereof Proclamation No. 84/2023, the Addis Ababa City Government Land Tenure Registration and Information Agency has issued this Directive.

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

1. **Short Title**

   This Directive may be cited as:"A Regulation to Provide for the Administration of Sport Facilities of the Addis Ababa City Government Regulation No.189/2024".

2. **Definition**

   Unless the context or the phrase otherwise requires in this Regulation:

   1. "**City**" means the Addis Ababa City;
   2. "**City Administration**" means Addis Ababa City Government;

፫. **“ቢሮ”** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ነው፤

፬. **“ስፖርት”** ማለት ማንኛውም ሰው ጤንነቱን ለመጠበቅ፤ ለመዝናናት፤ አካሉን ለመገንባትና አዕምሮን ለማበልጸግ እንዲሁም አቅምና ችሎታውን ለመመዘን በግሉ ወይም በጋራ በተደራጀ ወይም ባልተደራጀ ሁኔታ የሚያከናውነውን ማናቸውንም የአካል እንቅስቃሴ ነው፤

፭. **“የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ"** ማለት ለስፖርታዊ እንቅስቃሴ፤ ስልጠና፤ ውድድር፤ መዝናኛ ወይም ለስፖርታዊ በዓል ማከናወኛነት እንዲውል የተዘጋጀ ማንኛውም በመንግሥት የሚተዳደር ስፍራ ነው፤

፮. **“ህጋዊ ጥበቃ”** ማለት በከተማ አስተዳደሩ ማስተር ፕላን ለስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እንዲውሉ የተወሰኑ ስፍራዎችን ከታለመላቸው ዓላማ ውጭ እንዳይውሉ ማስጠበቅ ነው፤

፯. **“ደህንነት ማስጠበቅ”** ማለት የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ከተፈጥሮና ከሰው ሰራሽ አደጋዎች እንዲጠበቁ ማድረግ ነው፤

፰. **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፫. <u>**የፆታ አገላለፅ**</u>

በዚህ ደንብ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

፬. <u>**የተፈጻሚነት ወሰን**</u>

፩. ይህ ደንብ በከተማው አስተዳደር ባለቤትነት በሚተዳደሩ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፤

3. "**Bureau**" means the Youth and Sports Bureau of the Addis Ababa City Government;
4. “**Sport**” means any physical activity carried out by an individual or a group either in organized or unorganized manner for the purpose of maintaining health, recreation, physical fitness and cultivation of brain as well as for testing ones fitness and skill;
5. “**Sport facility**” means any facility established for sporting exercise, training, competition, and recreation or sporting events;
6. “**Legal protection**” means securing certain areas not to be used without their intended purpose in the city administration's master plan for sports facilities to be used;
7. “**Securing**” means keeping sports venues safe from natural and man-made disasters;
8. "**Person**" means any natural or juridical person.

3. <u>**Gender Expression**</u>

In this Regulation, any expression in the masculine gender shall include the feminine gender.

4. <u>**Scope of Application**</u>

1. This Regulation shall be applicable to any sport facility found in the Addis Ababa city government;

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም በሕዝብ መዝናኛ ፓርኮች ውስጥ የሚገኙ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ላይ ይህ ደንብ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

፭. **ዓላማ**

የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን በማስተዳደር እና ደህንነታቸውን በማስጠበቅ ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል በእኩልነትና በፍትሐዊነት አገልግሎት እንዲሰጡ ማስቻል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ዓይነት እና አስተዳደር

፮. **የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ዓይነቶች**

በከተማ አስተዳደሩ አገልግሎት የሚሰጥባቸው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩. የእግር ኳስ ሜዳ፤
፪. የቅርጫት ኳስ ሜዳ፤
፫. የቮሊቦል ሜዳ፤
፬. የእጅ ኳስ ሜዳ፤
፭. የቴኒስ ሜዳ፤
፮. የአትሌቲክስ ሜዳ፤
፯. የ፪ በ፩ የቅርጫት ኳስና ቮሊቦል ሜዳ፤
፰. የ፫ በ፩ የቅርጫት ኳስና ቮሊቦልና የእጅ ኳስ ሜዳ፤
፱. ጂምናዚየም፤
፲. የውሃ ዋና ገንዳ፤
፲፩.ሌሎች የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ዓይነቶች፡፡

2. Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, this Regulation may not apply to non-commercial sport facilities which are found in any individual residential premises.

5. **Objective**

Enabling all members of the public to serve equally and with a sense of integrity by managing sports facilities and keeping them safe.

## PART TWO

## TYPE AND ADMINISTRATION OF SPORT FACILITIES

6. **Types of Sports Facilities**

The following are the types of sports facilities in which services are provided by the city government:

1. Football Field;
2. Basketball Field;
3. Volleyball Field;
4. Handball Field;
5. Tennis Field;
6. Athletic Field;
7. Field of 2 in 1 basketball and volleyball;
8. Field of 3 by 1 basketball and volleyball and handball;
9. Gymnasium;
10. Water swimming pool;
11. Sports facility parks and other types of sports facilities.

**፯. የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራን ስለሚያስተዳድር አካል**

፩. በከተማው አስተዳደር ውስጥ ያሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች የሚተዳደሩት በቢሮው ይሆናል፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ቢሮው በማዕከል ደረጃ ራሱ ከሚያስተዳድራቸው ውጪ ያሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን የሚያስተዳድረውን የአስተዳደር እርከን ይወስናል፤

፫. በአካባቢው ማህበረሰብ የተሰሩ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች በራሱ በማህበረሰቡ የሚተዳደሩ ይሆናል፤

፬. ቢሮው በመንግሥት ይዞታ ስር እና በትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ለማህበረሰቡ አገልግሎት የሚሰጡበትን አሰራር ይዘረጋል፡፡

**፰. በማዕከል ደረጃ የሚተዳደሩ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች**

ቢሮው የሚከተሉትን የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በማዕከል ደረጃ ያስተዳድራል፡-

፩. በከተማ አስተዳደሩ ስር የሚገኙ የስፖርት ትምህርትና ስልጠና ማዕከላትን፣

፪. የስፖርት ልህቀት ማዕከላትን፣

፫. የስፖርት አካዳሚዎችን፣ እና

፬. ኢንተርናሽናል ስታዲየሞችን፡፡

**፱. የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ስለማስተዳደር**

በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራን የሚያስተዳድር አካል የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

7. **Administration Body of the Sports Facility**

1. Sports facilities in the city government will be managed by the Bureau;

2. Notwithstanding the provisions of Sub Article (1) of this Article, the Bureau at the center level itself determines the level of administration that governs the facilities of the sports facilities outside of what it administers;

3. Sports facilities made by the local community will be managed by the community itself;

4. The Bureau establishes a procedure under which sporting facilities located in public-owned and school facilities are used for the community.

8. **Center-level Administered Sports Facilities**

The Bureau administers the following sports facilities at the center level:

1. Sports education and training centers under city government;
2. Centers of Sports Excellence;
3. Sports Academies and
4. International Stadiums.

9. **Administering the Sports Facilities**

The body that administers a sports facility at any level will have the following duties and responsibilities:

፩. የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ አስፈላጊው ጥበቃ እንዲያገኝ ያደርጋል፣

፪. በስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ላይ ጉዳት የሚያደርስ፣ ሁከትና ብጥብጥ የሚፈጥረውን ማንኛውም ሰው ማስረጃ በማደራጀት ለፍትህ አካላት በመላክ ተጠያቂ እንዲሆን ያደርጋል፣

፫. የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ዕድሳትና ጥገና በሚያስፈልጋቸው ጊዜ ተከታትሎ ያስፈጽማል፣ይፈጽማል፣

፬. በስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች የሚሰጡ አገልግሎቶችን የማስፋፋትና ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ይከታተላል፣ ይደግፋል፣

፭. የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራው ለአካል ጉዳተኞች አገልግሎት ምቹ መሆኑን እና ተጠቃሚነታቸውን ያረጋግጣል፣

፮. ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ በሚሰጠው አገልግሎት ፍትሃዊ ተጠቃሚ መሆኑን ያረጋግጣል፣

፯. የመክፈል አቅም የሌላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እና ታዳጊ ወጣቶች ያለክፍያ አገልግሎቱን የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ተጠቃሚ መሆናቸውንም ያረጋግጣል፡፡

፲. **የአካባቢ ማህበረሰብ ስለሚያስተዳድራቸው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች**

የአካባቢ ማህበረሰብ የሚከተሉትን የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ያስተዳድራሉ፡-

፩. ማህበረሰቡ በሚኖርባቸው አካባቢዎች ላይ የመንግስት ይዞታ የሆኑ ጥርጊያ ሜዳዎችን እና

፪. በጋራ መኖሪያ ቤቶች አካባቢ የተገነቡ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች፡፡

1. It will ensure that a sports facility will receive the necessary protection;
2. It would organize the evidence of anyone who causes harm to the sporting facilities, creates violence, and send it to the judiciary to be held accountable;
3. When sporting facilities need to be restored and maintained, it will follow and execute;
4. It monitors and supports the expansion and standardization of services provided in sports facilities;
5. The sports facility ensures that the facilities are suitable for the services of the disabled and ensures their use;
6. It ensures that all members of the public benefit fairly from the services provided by the sporting facility;
7. It facilitates the access to the services of members of the public and a teenager who cannot afford to pay, and ensures that they are beneficiaries.

10. **Sports Facilities Administered by the Local Community**

The local community administers the following sports facilities:

1. Paved meadows that are state-owned on the areas where the community resides, and
2. Sport facilities built in a shared housing area.

**፲፩. የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች የግንባታ ስታንዳርድ**

፩. የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ስታንዳርድ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች አስተዳደርን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፯፻፳፱/፪ሺ፬ አንቀፅ ፬ መሰረት የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች አመዳደብ እና በኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ ስታንዳርድ መሠረት ይሆናል፤

፪. የአካባቢ ማህበረሰብ የሚያስተዳድራቸው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ስታንዳርድ ቢሮው በሚያወጣው ደረጃ ይሆናል፡፡

**፲፪. የአካባቢ ማህበረሰብ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ አስተዳደር**

የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራን በመረከብ የሚያስተዳድር ማንኛውም የማህበረሰብ አደረጃጀት የሚከተሉትን የአስተዳደር ተግባራት ያከናውናል፡-

፩. የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራው አገልግሎቶች ለሁሉም ተገልጋይ በእኩልነትና በፍትሐዊነት እንዲሰጡ ያደርጋል፤

፪. ለታዳጊ ወጣቶች የጊዜ ማሳለፊያ ሆነው እንዲያገለግሉ አስፈላጊ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤

፫. የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራውን ያለማል፤ ያስፋፋል፤ይጠብቃል ፤ይንከባከባል፤

፬. የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራው ከታለመለት ዓላማ ውጪ እንዳይውል ይቆጣጠራል፤

፭. የአገልግሎት አሰጣጣጡ እንዲሻሻል ያደርጋል፤

**11. Construction Standard for Sports Fields**

1. The standard for sports facilities shall be in accordance with Article 4 of Proclamation No. 729/2012 on the determination of the management of sports facilities, the classification of sports facilities and the standard of the Ethiopian Standards Agency;
2. The sports facilities that the local community administers will be at the level that the Standard sets out by the Bureau.

**12. Local Community Sports Field Administration**

Any community organization that governs by taking over the sport field area performs the following administration functions:

1. The sports facility will ensure that services are provided to all beneficiaries on equal and fair terms;
2. It creates the necessary amenities for teenagers to serve as a pastime;
3. A sports facility will not dream of the venue, it will expand, it will wait and take care of it;
4. A sports facility controls the venue from being used against its intended purpose;
5. It will cause the service delivery to improve;

፮. በስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራው ላይ ጉዳት እንዳይደርስ አስቀድሞ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ይወስዳል፤ ጉዳት ሲያጋጥም በፍጥነት ወደነበረበት ሁኔታ እንዲመለስ ያደርጋል ወይም ጉዳቱ ጉዳት ያደረሰ ሰው ወደ ነበረበት እንዲመልስ ያደርጋል፤

፯. ወቅታዊ ጥገና እና እድሳት እንዲከናወን ያደርጋል፡፡

## ክፍል ሦስት
## የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ስለሚሰጧቸው አገልግሎቶች

**፲፫. ስለ ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች አገልግሎት**

የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እንደየሁኔታው የሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

፩. ለስፖርታዊ ስልጠና፣ ለስፖርታዊ ውድድር፣ ለማህበረሰብ አቀፍ የአካል ብቃት ስፖርታዊ እንቅስቃሴ፤

፪. ለስፖርታዊ መዝናኛ ወይም ለስፖርታዊ በዓል ማከናወኛ፤

፫. ለታዳጊዎች፤ በየደረጃው ለሚገኙ የስፖርት ቡድኖች፤ ክለቦችና ለሙያ ማሻሻያ የሚሆን የስልጠና አገልግሎት መስጠት እና ለስፖርታዊ ልምምድ፤

፬. ለታዳጊዎች፤ በየደረጃው ለሚገኙ የስፖርት ቡድኖች፤ ክለቦች፤ የወረዳዎችና የክፍለ ከተሞች የውስጥ ውድድር፤ ከተማ አቀፍና ሀገር አቀፍ ውድድሮችና ፌስቲቫሎች የውድድር አገልግሎት፡፡

**፲፬. በጂምናዚየም**

ጂምናዚየሙ የሚሰጠው አገልግሎት፡-

6. In order to avoid damage to the sports facility, it will take precautionary measures in advance, in the event of injury, quickly restore it to its original state, or cause the injury to reinstate a person who has caused an injury;

7. It will result in periodic maintenance and restoration taking place.

## PART THREE
## SERVICES PROVIDED BY SPORT FACILITIES

**13. Service of Sports Facilities**

Sports facilitiess will be as follows, with the services provided on a case-by-case basis:

1. For sports training, sports competition, community-based fitness workout;
2. Performing for sports entertainment or a sporting holiday;
3. For teenagers, for sports teams at all levels, to provide clubs and training facilities for professional improvement and for sports practice;
4. For teenagers, for sports teams at all levels, clubs, internal competitions of Woredas and Sub-Citys competitive services for citywide and national competitions and festivals.

**14. At the Gymnasium**

The services the gymnasium offers are:

፩. ለታዳጊዎች፤ በየደረጃው ለሚገኙ የስፖርት ቡድኖችና ክለቦች ቮሊቦል፤ ቅርጫት ኳስ፣ እጅ ኳስ፣ ጠረጴዛ ቴኒስ ፣አርት ስፖርትና ባድሚንተን ለሙያ ማሻሻያ፣ ልምምድ፣ ስልጠና፣ ውድድርና ስፖርታዊ ፌስቲቫል፤ እና

፪. በመሳሪያ የተደገፈና ያለመሳሪያ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ለሁሉም ማህበረሰብ ክፍል አገልግሎት፤ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት

## የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ተጠቃሚዎች መብትና ግዴታ

**፲፭.የተጠቃሚዎች መብት**

ተጠቃሚዎች፡-

፩. በስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በልማት ተግባራት የመሳተፍ መብት፤

፪. በተቀመጠላቸው ፕሮግራም መሰረት አገልግሎት የማግኘት መብት፤

፫. በእኩልነትና በፍትሐዊነት የመገልገል መብት፤

፬. በስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ የወጣውን የአጠቃቀም ፕሮግራም የማወቅ መብት አላቸው፡፡

**፲፮.የተጠቃሚዎች ግዴታ**

ተጠቃሚዎች የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን፡-

፩. የሚያስተዳድረው አካል የሚያወጣቸውን የአጠቃቀም ፕሮግራሞች የማክበር፤

፪. ደህንነት የመጠበቅ፤

፫. ንብረት እንዳይባክንና እንዳይበላሽ የመንከባከብ፤

1. For teenagers; volleyball for sports teams and clubs at all levels; basketball, handball, table tennis, art sports and badminton for professional improvisation, practice, training, competition and sports festival; and
2. It will be Instrumented and un-instrumental exercise for the service of a class of all communities.

## PART FOUR

## RIGHTS AND OBLIGATION OF USERS OF SPORT FACILITIES

15. **Users' Rrights**

Users:

1. Right to participate in development activities at sports relay locations;
2. Right to service according to the program they are placed in;
3. Right to serve in equality and justice;
4. They are entitled to know the use program that was put out in a sports relay.

16. **Obligation of Users**

Users sports facilities:

1. Respecting the use programs that the governing body issues;
2. Keeping the Security;
3. To take care of property to prevent it from being wasted and ruined;

፬. ጉዳት እንዳይደርስባቸው ወይም ሁከት ሊያስነሳ ከሚችል ማንኛውም ድርጊት የመከላከል፤
፭. የሚያስተዳድረው አካል የሚያወጣቸውን መመሪያዎችና አሰራሮች የማክበር፤
፮. በአጠቃቀም ጉድለት ምክንያት የደረሰውን ጉዳት የማስተካከልና ወደነበረበት የመመለስ፤
፯. ተቃራኒ ሁኔታ ከሌለ በቀር ለሚያገኘው አገልግሎት የተወሰነውን ክፍያ የመፈጸም፤
፰. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) የተደነገገው ቢኖርም ታዳጊ ወጣቶች እና አካል ጉዳተኞች የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ አገልግሎት ክፍያ አይፈጽሙም፡፡

## ፲፯. ተገልጋዩ ማሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታዎች

፩. ከስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ዓላማ ጋር የማይጣረስ የስፖርት ትጥቅ ማሟላት፤
፪. የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራን የሚያስተዳድረው አካል ከሚያወጣው ፕሮግራም ውጪ ለመገልገል ከሶስት ቀን በፊት አስቀድሞ የአገልግሎት ጥያቄ ማቅረብ፤
፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት ከፕሮግራም ውጪ ለመገልገል የሚያስተዳድረው አካል ያወጣውን ፕሮግራም የማያስተጓጉል ሆኖ ሲገኝ ይሆናል፤
፬. የተለያዩ በስፖርት የተደራጁ ቡድኖች፤ ክለቦች፤ ፌዴሬሽኖችና ኮሚቴዎች ዓመታዊ ፕሮግራማቸውን አስቀድሞ ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል፤
፭. ክፍያ ለሚያስፈልጋቸው አገልግሎቶች አስቀድሞ ክፍያ መፈፀም፡፡

4. To defend against any action that might cause harm or provoke violence;
5. To comply with the directives and procedures issued by the party administering them;
6. To repair and restore damage caused by lack of use;
7. To make a portion of the payment for the service he receives unless there is a contrary situation;
8. Despite the provisions of Sub Article (7) of this Article, teenagers and people with disabilities do not make payments for the use of the sports facilities.

## 17. Preconditions that the User Must Meet

1. Complementing a sports armature that is not in conflict with the purpose of a sports relay facility;
2. To submit a request for service in advance of three days in order to serve outside of the program that the party running the sports facility will produce;
3. According to Sub Article (2) of this Article, it would be when the governing body for off-program use would be found to not interfere with the program it had put out;
4. Various sports-organized teams; clubs, federations and committees are required to announce their annual programme in advance;
5. Fee-making in advance for services that require payment.

፲፰. **የአጠቃቀም ፕሮግራም ስለማውጣት**

፩. የአጠቃቀም ፕሮግራም በየደረጃው የሚገኙ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን የሚያስተዳድሩ አካላት በሚያወጡት መሠረት ይሆናል፤

፪. የአጠቃቀም ፕሮግራም ሲወጣ ቅድሚያ ሊሰጥ የሚገባው ከወረዳ እስከ ከተማ ለሚካሄዱ የተለያዩ ስፖርታዊ ክንዋኔዎች ይሆናል፤

፫. በተቋሙ የሚመሩ ድንገተኛ ስፖርታዊ ተግባራት ሲያጋጥም የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራው አስቀድሞ በክፍያ ቢያዝም ፕሮግራሙን ያሽጋሽጋል ወይም ይሰረዛል፤

፬.የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራውን የአጠቃቀም ፕሮግራም ያወጣው አካል ፕሮግራሞቹን ለተጠቃሚው ማህበረሰብ በማስታወቂያ ሰሌዳ በመለጠፍ ወይም ደብዳቤ በመጻፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

፲፱. **ስለአገልግሎት አሰጣጥ**

፩. የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል በእኩልነትና በፍትሐዊነት አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፤

፪. በመንግስታዊ ተቋማት ውስጥ የሚገኙ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች የአሰራር ሥርዓትን ተከትለው አገልግሎት የሚሰጡበትን ሁኔታ ማመቻቸት፡፡

፳. **ለስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ህጋዊ ጥበቃ**

የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን፡-

፩. በከተማው ማስተር ፕላን የተመላከቱ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ማስጠበቅ፤

18. **Issuing the Use Program**
    1. A usability program will be based on what the entities that manage the sports relay facilities at each level will issue;
    2. When a use program is introduced, the priority should be given to various sporting events that take place from woreda to city;
    3. In the event of emergency sporting activities run by the facility, the sports facility will either be reprogrammed or cancelled, even if the facility is already booked for a fee;
    4. The party that sets out the sports facility's use program will have to inform the user community by posting the programs with a billboard or writing a letter.
19. **Service Delivery**
    1. To ensure that sporting facilities are provided to all members of the public through equal and fair service;
    2. Facilitating the conditions under which sports venues in governmental institutions are serviced following a system of procedures.
20. **Legal Protection of Sports Facilities**

    Sports facilities:

    1. Securing sports facilities that were flagged by the city's master plan;

፪. ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲያገኙ ተገቢውን ክትትል ማድረግ፤

፫. ሊጎዱ የሚችሉ ማንኛውም ተግባር እንዳይከናወን ማድረግ፤

፬. አስቀድሞ መከላከል የሚቻል የተፈጥሮ አደጋዎችን ለመከላከል አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ማድረግ፤

፭. ከአጠቃቀም ጉድለት ለሚደርስ ጉዳት ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፡፡

፳፩. **የመንግስትና የግል ዘርፉ ትብብርን ስለመፍጠር**

ቢሮው ከግል ዘርፉ ጋር በመንግስት እና ግል አጋርነት ስለሚሰራበት ሁኔታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስትና ግል አጋርነት ሕግ መሰረት ይሆናል፡፡

፳፪. **አገልግሎት በውል ለሦስተኛ ወገን ስለማስተላለፍ**

ቢሮው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች አገልግሎት በውል ለሦሰተኛ ወገን ከፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ቢሮ ጋር በመነጋገር መሰረት ያስተላልፋል፡፡

**ክፍል አምስት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

፳፫. **ክልከላ**

በስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ውስጥ፡-

፩. ከተፈቀደው ዓላማ ውጭ ለሌላ አገልግሎት መጠቀም ወይም ለሺሻ ማስጨሻ ወይም ለጫት ማስቃሚያ አገልግሎት ማዋል፤

፪. ጉዳት የሚያደርስ ወይም አምባጎሮ ወይም ጠብ መፍጥር ወይም ሁከት ሊያስነሳ የሚያስችል ድርጊት መፈጸም፤

2. Providing appropriate supervision for them to obtain a valid proof-of-possession map;
3. To prevent any action that may be affected from taking place;
4. Making the necessary preparations to prevent pre-emptive natural disasters;
5. To ensure that appropriate sticking action is taken for damage from loss of use.

21. **Making of Cooperation in the Public and Private Sector**

The status of the office in public-private partnership with the private sector will be in accordance with the Addis Ababa City Government Public-Private Partnership law.

22. **Outsourcing the Service to a third party**

The Bureau also communicates the services of sports facilities to the counterfeit party on a contract basis with the Public Service and Human Resources Development Bureau.

**PART FIVE**

**MISCELLANEOUS PROVISIONS**

23. **Restrictions**

In sports facilities:

1. Use for other uses other than the permitted purpose; or for smoking shisha or chewing chat;
2. To commit an act that causes harm or can cause fighting or quarrels or provoke violence;

፫. ለመልካም ሥነ-ምግባር ተቃራኒ የሆኑ ወይም የአልኮል መጠጥ ማስታወቂያ የወጡ ሕጎችን በመተላለፍ መለጠፍ፤ የአልኮል መጠጥ እና ሱስ የሚያሲዙ ዕጾችን ይዞ መግባት ወይም መጠቀም፤ ቁማርና ሌሎች አስነዋሪ ተግባራትን በስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራው ውስጥ መፈፀም፤

፬. የተቀመጡ የጥንቃቄ እርምጃዎችን፣ መመሪያዎችና ክልከላዎችን አለመተግበር፤

፭. የጦር መሳሪያ፣ ስለታማ፣ ተቀጣጣይ የሆኑ ቁሶችን እና መርዛማ ፈሳሾችን ይዞ መግባት፤

፮. የሚከራዩ ሱቆችና ንግድ ቤቶች ኪራይ ከተፈቀደው የግዥ ዘዴ ወይም ከተቀመጠው የአገልግሎት ክፍያ ውጭ ማከራየት ወይም ማስከፈል፤

፯. ለሕዝብ ጥምቅ ሲባል በሕግ በተደነገገው መሠረት ካልሆነ ወይም የከተማው አስተዳደር ካቢኔ ካልፈቀደ በስተቀር ይዞታውን መውሰድ ወይም ለሌላ አገልግሎት እንዲውል ማድረግ፤

፰. ሌሎች በዚህ ደንብ የተደነገጉ ድንጋጌዎችን አሰራሮች ውጭ መጠቀም ወይም አገልግሎት መስጠት፤

የተከለከለ ነው፡፡

## ፳፬. የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ የገቢ ምንጭ

፩. የገቢ ምንጭ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ) ከስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ጋር የተገነቡ ሱቆች ኪራይ፣

3. Posting for violations of laws that are contrary to good ethics or advertised for alcohol consumption; entering or using alcohol and addictive literature; performing gambling and other abusive activities in the sports remortgage area;
4. Non-implementation of established precautionary measures, directives and restrictions;
5. Firearms, carrying sharp, flammable materials and toxic liquids;
6. Rent-for-hire shops and businesses may be used outside of the approved method of purchase or the set service fee, or to rent or charge;
7. To take possession or to have it used for other purposes, unless it is in accordance with the provisions of law for the purpose of public interest, or if the cabinet of the city government permits it;
8. It is forbidden other use or service outside the procedures of provisions made by this Regulation.

## 24. The Source Income of Sports Facility

1. The source of income will be as follows:
   a) Rental Shops Built with Sports Fields;

ለ) ከስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ከሚገኝ የአገልግሎት ክፍያ፣ እና

ሐ) ከግል ድርጅቶች፣ ባለሃብቶች፣ ከነዋሪው ከሚገኝ ድጋፍና ስጦታ፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚገኘው ሀብት በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር ሕግ መሰረት ለስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራው አስተዳደር ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

**፳፭. <u>ስለሚከራዩ ሱቆችና የአገልግሎት ክፍያ</u>**

የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ፡-

፩. የሚያከራያቸው ሱቆች ወይም ንግድ ቤቶች የኪራይ ዋጋ የሚወሰነው በሚወጣ ግልጽ ጨረታ ይሆናል፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ተጫራች ካልቀረበ በሌሎች የጨረታ ዘዴዎች በማወዳደር ይሆናል፤

፫. ለሚሰጧቸው አገልግሎቶች የተጠቃሚውን ወይም የተገልጋዩን አቅም ያገናዘበና ተመጣጣኝ የሆነ የአገልግሎት ክፍያ መሆን ይኖርበታል፡፡

**፳፮. <u>የንብረት አስተዳደር</u>**

ቢሮው ወይም ጽህፈት ቤቶች የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን በከተማው አስተዳደር የንብረት አስተዳደር ህግ መሰረት ንብረቶቹን ያስተዳድራሉ፡፡



b) From a service fee located at the sports facility; and

c) From private enterprises, investors, support and donations from the resident.

2. According to Sub Article (1) of this Article, the resources available will be made available for use by the administration of the sports area under the City Government's Financial Management Law

**25. <u>Shops that are Rented and Service Fees</u>**

Sporting Facilities:

1. The rental value of the shops or businesses it rents will be determined by a clear auction that will be issued;
2. Under Sub Article (1) of this Article, a bidder will be able to compete with it by other bidding methods if it is not offered;
3. For the services they provide, it must be a service fee that takes into account the capabilities of the user or consumer and is affordable.

**26. <u>Property Administration</u>**

The Bureau or offices administer the sports facilities under the City Government Property Administration Law, which states.

**፳፯. <u>ስለተጠያቂነት</u>**

ማንኛውም ሰው የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የጣሰ ወይም አፈጻጸሙን ያሰናከለ ወይም የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን ሀብትና ገንዘብም ሆነ ንብረት ያባከነ ወይም ያጎደለ ወይም ያበላሸ እንደሆነ አግባብ ባላቸው የወንጀልና የፍትሐ-ብሔር ህጎች መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**፳፰. <u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች</u>**

ይህን ደንብ የሚቃረን ማናቸውም የከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ ያወጣው ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፳፱. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ ከህዳር ፱ ቀን ፪ሺ፲፯ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ከህዳር ፱ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

27. **<u>Liability</u>**

Anyone who violates or disables the provisions of this regulation, or waste or damage or lacking the resources and money or property of the sports facilities is liable under appropriate criminal and civil laws.

28. **<u>Inapplicable Laws</u>**

Any regulation, directive or customary practice of the City Cabinet does not apply to issues covered by this Regulation.

29. **<u>Effective Date</u>**

This regulation shall enter into force as of November 18, 2024.

**Done at Addis Ababa this 18 th day of November 2024.**

**Adanech Abiebie**

**Mayor of Addis Ababa City**